

በ: ታሚ ሃርኤል
ምሳሌዎች: ዔናት ጻራፋቲ
הוֹצָאָה: זברה
የእድሜ ክልል: ቅድመ ትምህርት ቤት

שִׂיחָה

ከታሪኩ ወደኛ

ምሥሎችን አንድ ላይ በማየት፣ በታሪኩ ውስጥ ያሉትን የልጆቹን ድርጊትና የፊት ገጽታ ትኩረት እያደረጉ መጠየቅ ይችላሉ፡- ምን ይሰማቸዋል? መቼ ነው የሚዝናኑት? ተናደዋል? ልጅቷ "የበለጠች" መሆን የምትፈልገው ለምን ?ይመስላችኋል? አንድ ሰው "እኔ እበልጣለሁ" ሲል ምን ይሰማችኋል

מִשְׂחָק

እበልጣለሁ"ን መተወን"

ታሪኩን አንድ ላይ መተወን ይችላሉ፡-እንቅስቃሴዎቹን በምሥሎች ውስጥ ይፈልጉና ሚናዎችን በመቀያየት የራሥዎን ዓረፍተ ነገር ያክሉ። ለምሣሌ፡- ከመካከላችሁ አንዱ "የሆነ ታሪክን ከአንተ ጋር ማንበብ እወዳለሁ" ቢል ሌላኛው ደግሞ "እኔ ካንተ የበለጠ!" ሊል ይችላል።

מִשְׂחָק

የበለጠ መፈለግ

ቤቱ ዙሪያ አጫዋችና ፈታኝ ጨዋታን በሚጫወቱበት ጊዜ ቋንቋውን በተለያዩ ቅጽሎች ያበለጽጉ። ቤት ውስጥ የሚገኝን ዕቃ ይምረጡ። በመረጡት መግለጫ መሰረት እንዲህ ብለው ይጠይቁ፦ “ማን ነው የበለጠ ...” ትልቅ/ትንሽ/ግልጽ/ባለ ቀለምና የመሣሠሉት። ሌላኛው ተሥታፊ አንድ አይነት ነገርን ግን “የበለጠውን” ይፈልጋል። .ለምሣሌ፦ ትልቅ ኳስ፣ ለስላሳ ትራስ፣ ወዘተ

שִׂיחָה

በእኛው ቃላት

ጥቂት ቃላት ያሏቸው መጻህፍት ዕድል ይይዛሉ! ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ ልጆቹ በምሥሎቹ ላይ ተመስርተው ታሪኩን በራሳቸው ቃላት እንዲናገሩ መጠየቅ ይችላሉ። ልጆቹ ታሪኩን የሚናገሩበት መንገድ ውስጣዊውን ዓለም ለማየት እንዲችሉ ያደርጋል።

מִשְׂחָק

QR ኮድ

ኮዱን ስካን በማድረግ “እኔ እበልጣለሁ!” የሚለውን ጨዋታ ይጫዎቱ። መመሪያዎቹ ከውስጥ ናቸው – ብቻ !ፕሪንት በማድረኛ በመቆራረጥ አብረው ይዝናኑ

הַשְׁרָאָה

ፒንተረስት

ተጨማሪ ስራዎች፣ ግጥሞችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ